# ትንቢተ ሚልክያስ

## መግቢያ

### ጸሐፊው

ጸሐፊው ሚልክያስ እንደ ሆነ ይነገራል፤ የስሙም ትርጉም፣ "መልእክተኛዬ" ማለት ነው:: ይኸው ቃል በ3፥1 ላይ በመገኘቱና ነቢያትም ሆኑ ካህናት፣ የጌታ መልእክተኞች እንደ መሆናቸው (2፥7፤ሐጌ 1፥13 ይመ) አንዳንድ ሰዎች፣ "ሚልክያስ" የሚለውን መጠሪያ ሕዝቡ በልማድ ብቻ ለጸሐፊው የሰጠው ስም ነው ይላሉ:: ለዚህ አመለካከታቸው ዋቢ አድርገው የሚያቀርቡት የጥንቱን የሰብዓ ሊቃናት የግሪክ ትርጉም ነው፤ ምክንያቱም ይህ ትርጉም በ1፥1 ላይ የሚገኘውን የተጸውዖ ስም በማድረግ ፈንታ እንዲሁ "መልእክተኛው" ብሎታል::

### ታሪካዊ ዳራው

ከምርኮ የተመለሱት ወገኖች በሐጌና በዘካርያስ ትንቢታዊ እንቅስቃሴ ተነሣሥተው፣ የቤተ መቅደሱን ሥራ በገዛቸው በዘሩባቤል መሪነት በ516 ዓ.ቅ.ክ አጠናቀቁ:: በ458 ዓ.ቅ.ክ ካህኑ ዕዝራና በሺህ የሚቈጠሩ አይሁድ ከምርኮ በመመለሳቸው ማኅበረሰቡ ተበረታቶአል:: ዕዝራ... የሚካሄደውን አምልኮ ፈርጅ አስይዞ እንዲያዳብረውና (ዕዝ 7፥17) የሙሴም ሕግ በመታዘዝ ሥራ ላይ መዋሉን እንዲያረጋግጥ (ዕዝ 7፥25-26)፣ የፋርሱ የንጉሥ አርጤክስስ ዕዝራን አበረታታው::

ከዐሥራ ሦስት ዓመት በኋላም (445 ዓ.ቅ.ክ)፣ ይኸው የፋርስ ንጉሥ ጠጅ አሳላፊው ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስና ቅጥሮቹን እንደ ገና እንዲሠራ ፈቀደለት (ነህ 6፥15):: ነህምያ አዲስ የተሾመ ገዥ እንደ መሆኑ መጠን፣ ድኾች የሚረዱበትን መንገድ በመቀየስ ረገድ ግምባር ቀደም ስፍራን ያዘ (ነህ 5፥12-13)፤ ከዚህም በላይ ከባዕድ ሕዝብ ጋር የሚፈጸመው ጋብቻ ዕርም ተብሎ እንዲቀር፣ ሰንበት እንዲከበር (ነህ 10፥30-31)፣ ዐሥራትና መባቸውንም በታማኝነት እንዲከፍሉ (ነህ 10፥37-39) ሕዝቡን አግባባ::

ነህምያ በ433 ዓ.ቅ.ክ የፋርስን ንጉሥ ለማገልገል ወደዚያ ተመለሰ፤ የአይሁድ ሕዝብም እርሱ በሌለበት ወቅት እንደ ገና በኀጢአት ወደቀ:: ኋላ ግን ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም በተመለሰ ጊዜ፣ ዐሥራት መክፈል እንደ ቀረ፣ ሰንበት እንደ ተሻረ፣ ሕዝቡም ከባዕዳን ሕዝቦች ጋር እንደ ተጋቡና ካህናቱም በምግባረ ብልሹነት እንደ ተበከሉ (ነህ 13፥7-31) ተመለከተ:: ከእነዚህ በደሎች ብዙዎቹን ነቢዩ ሚልክያስ አውግዞአል (1፥6-14፤ 2፥14-16፤ 3፥8-11 ይመ)::

### የተጻፈበት ጊዜ

ነህምያና ሚልክያስ ያወገዟቸው የሕዝቡ በደሎች ተመሳሳይ መሆናቸው፣ ሁለቱም መሪዎች በአንድ ዘመን እንደ ነበሩ ያመከታል:: ትንቢተ ሚልክያስ በ433 ዓ.ቅ.ክ ነህምያ ወደ ፋርስ ከተመለሰ በኋላ ወይም ለሁለተኛ ጊዜ ገዥ ሆኖ በተሾመበት ጊዜ ተጽፎ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ በ1፥8 የተጠቀሰው ገዥ (የዚህኑ ማብ ይመ) ነህምያ ላይሆን ስለሚችል፣ የመጀመሪያው አማራጭ እውነት ላይሆን አይቀርም:: ሚልክያስ የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ነቢይ ላይሆን አይቀርም (አንዳንዶች ግን ኢዩኤልን ከእርሱ በኋላ የተነሣ ነቢይ አድርገው ይቈጥራሉ)::

### የመጽሐፉ መሪ ሐሳብና ትምህርተ መለኮት

አይሁድ ከምርኮ ተመልሰው ቤተ መቅደሱን እንደ ገና እንዲሠሩ ቢፈቅድላቸውም እንኳ፣ አንዳንድ ተስፋ አስቈራጭ ሁኔታዎች በሃይማኖታቸው ላይ ሕጸጽ አስከትለዋል፤ (1) ምድራቸው በፋርስ ሰፊ ግዛት መካከል ተገልላ የተቀመጠች አነስተኛ ክፍለ አገር ሆና ቀርታለች፤ (2) በነቢያቱ (ሌሎች ይደጎረ ምርኮ ነቢያትን ሐጌንና ዘካርያስን ጨምሮ) የክብር ዘመን ወደፊት እንደሚመጣ የተተነበየው ትንቢት አልተፈጸመም፤ (3) አምላካቸው በመዝ 68 እንደ ተመለከተው በአሕዛብ ፊት መንግሥቱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ሲል በኀይልና በግርማ ወደ መቅደሱ አልመጣም (3፥1):: ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔርን የፍቅር ኪዳን በመጠራጠርና (1፥2) በፍትሕ ሰጪነቱ ባለመታመን (2፥17፤ 3፥14-15)፣ ወደ ምድሩ የተመለሰው የአይሁድ ማኅበረ ሰብ ተስፋ መቍረጥ ጀመረ:: አምልኮአቸው ከዘመን ዘመን እንዲሁ የሚጓዙበት ሃይማኖታዊ ሥርዐት ብቻ ሆነ፤ ሕጉንም በጥንቃቄ ማክበሩን ገሸሽ አደረጉ::

ሚልክያስ ካህናቱና (1፥6-2፥9) ሕዝቡ (2፥10-16) የእግዚአብሔርን ፍቅር እየተጠራጠሩ (1፥2-5)፣ እምነተ ቢሶች በመሆናቸው ይወቅሳቸዋል::እግዚአብሔር ኢፍትሐዊ ነው፤ ሕዝቡንም ከፍ ከፍ ያደርግ ዘንድ በፍርድ አልመጣም ("የፍርድ አምላክ ወዴት አለ?" 2፥17)፤ በማለት ያቀረቡትን ክስ ሚልክያስ በግልጽ በመናገርና በማስጠንቀቅ ይመልሳቸዋል:: እንዲመጣ የፈለጉት ጌታ በእርግጥ ይመጣል፤ ሆኖም "እንደ አንጥረኛ እሳት" (3፥1-4) ሆኖ ነው:: ለፍርድ መምጣቱ የማይቀር ነው፤ ነገር ግን ፍርዱ በመጀመሪያ በሕዝቡ ላይ ይፈጸማል (3፥5)::

ጌታ የገባውን ቃልና የነደፈውን ዕቅድ እንደ ሰው የማያጥፍና የማይሰርዝ አምላክ በመሆኑ፣

በተደጋጋሚ ከእምነት ያፈነገጠችውን እስራኤልን ጨርሶ አይተዋትም (3፥6)። ይሁን እንጂ፣ እስራኤል የእግዚአብሔርን በረከት እንደ ገና የምታገኘው (3፥6-12)፣ ሕይወቷን በንስሐ ስታድስ ብቻ ነው። ጌታን የሚያከብር ሁሉ እርሱ ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ ከጥፋት ያመልጣሉ (3፥16-18)።

በመደምደሚያም ሚልክያስ እንደ ገና "ያ ታላቅና አስፈሪ ቀን ይመጣል (4፥5)፤ እንደ ምድጃ እሳትም ያቃጥላል" (4፥1) በማለት ለአንባቢዎቹ ያረጋግጥላቸዋል፤ ያስጠነቅቃቸዋልም። በዚያን ቀን ጻድቃን ሐሤት ያደርጋሉ፤ "እናንተም ክፉዎችን ትረግጣላችሁ" (4፥1-3)። ስለዚህ "የባሪያዬን የሙሴን ሕግ ልብ በሉ" (4፥4)። ሕዝቡን ለዚያ ቀን ለማዘጋጀትና ወደ ቀደሙት አባቶቻቸው የጽድቅ መንገድ ለመመለስ ጌታ "ነቢዩን ኤልያስን" ይልካል፤ (4፥5-6)።

### ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያት

ትንቢተ ሚልክያስ፣ "ንግር" ይባላል (1፥1 እና ማብ ይመ)፤ በአጻጻፍ ረገድ ሲታይም ከፍተኛ ደረጃ ያለው የስድ ንባብ ጽሑፍ ነው። በጽሑፉ ውስጥ በእግዚአብሔርና በሰዎች አንደበት የቀረቡ ተከታታይ ጥያቄዎች ጐልተው ይታዩበታል። ብዙው ጊዜ ጌታ ሲናገር፣ "እናንተ ግን እንዲህ ብላችኋል" (1፥2፡6-7፤ 2፥14፡17፤ 3፥7-8፡13 ይመ፤ ከ1፥13 ጋር ያነጻጽሩ) የሚል የምፀት ቃል ይከተለዋል፤ ለእያንዳንዱም ጌታ መልስ ይሰጣል።

ድግግሞሽ የመጽሐፉ ዋኛ ባሕርይ ነው። "እግዚአብሔር ጸባኦት" የሚለው መጠሪያ ሃያ ጊዜ ተጽፎ ይገኛል። መጽሐፉ የኤዶምያስ ጠፍ ምድር ምን እንደሚመስል በመግለጽ ይጀምርና (1፥3-4)፣ እስራኤል ጥፋት እንዳይደርስባት በማስጠንቀቅ ይደመድማል (4፥6)።

በትንቢተ ሚልክያስ ውብ አባባሎች በብዛት ይገኛሉ። ካህናቱ በጌታ መሠዊዕት ላይ በንቀት ጢቅ አለብት (1፥13)፤ ጌታም መሥዋዕታቸውን ፋንድያ በፊታቸው ላይ ይበትናል (2፥3)። ጻድቅ ፈራጅ እንደ መሆኑ መጠንም፣ "እንደ አንጥረኛ እሳትና እንደ አጣቢ ሳሙና ይሆናል" (3፥2)፤ ለጻድቃን ግን "የጽድቅ ፀሐይ በክንፎቿ ፈውስን አዝላ ትወጣለች፤ እናንተም ወጥታችሁ ከጋጡ እንደ ተለቀቀ ጥጃ ትፈነጫላችሁ" (4፥2)።

### አስተዋፅኦ

1. ርእስ (1፥1)
2. መግቢያ፤ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው የኪዳን ፍቅሩ መረጋገጡ (1፥2-5)፤
3. እስራኤል ታማኝ ሆና ባለመገኘቷ ተግሣጽ ደረሰባት (1፥6-2፥16)

ሀ. የካህናቱ ታማኝ አለመሆን (1፥6-2፥9)
  (1) በመሥዋዕታቸው እግዚአብሔርን አላከበሩም (1፥6-14)
  (2) ሕጉን በታማኝነት አላስተማሩም (2፥1-9)

ለ. ሕዝቡ ታማኝ ሆነው አለመገኘታቸው (2፥10-16)

4. የጌታ መምጣት መታወጁ (2፥17-4፥6)

  ሀ. ጌታ ካህናቱን ለማንጻትና በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ ይመጣል (2፥17-3፥5)።
  ለ. ከጌታ መምጣት አንጻር ሕዝቡ ንስሐ እንዲገባ የቀረበ ጥሪ (3፥6-18)
    (1) የሕዝቡ ስጦታ በታማኝነት እንዲሆን የተሰጠ ምክር (3፥6-12)
    (2) ሕዝቡ በታማኝነት እንዲያገለግል የተሰጠ ምክር (3፥13-18)

ሐ. የጌታ ቀን መምጣት አይቀሬ መሆኑ በግልጽ ተናገረ (ም 4)

1 በሚልክያስ[ሀ] በኩል ወደ እስራኤል የመ
ጣው የእግዚአብሔር ቃል ንግር ይህ ነው፤

## ያዕቆብ ተወደደ፤ ዔሳው ተጠላ

2“እኔ ወድጃችኋለሁ” ይላል እግዚአብሔር፤
“እናንተ ግን፣ ‘እንዴት ወደድኸን?’ ትላላችሁ::
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “ዔሳው የያዕ
ቆብ ወንድም አልነበረምን? ያዕቆብን ወደድ
ሁት፤ 3ዔሳውን ግን ጠላሁት፤ ተራሮቹን
ባድማ አደረግሁ፤ ርስቱንም ለምድረ በዳ
ቀበሮዎች ሰጠሁበት::”
4ኤዶምያስ፣ “ብንደመሰስም እንኳ የፈረሰውን
መልሰን እንሠራዋለን” ይል ይሆናል:: እግዚ
አብሔር ጸባኦት ግን እንዲህ ይላል፤ “እነ
ርሱ ይሠሩ ይሆናል፤ እኔ ግን አፈርሰዋ
ቸዋለሁ፤ ክፉ ምድር፣ እግዚአብሔርም ለዘላለም
የተቈጣው ሕዝብ ተብለው ይጠራሉ:: 5ይህንም
በገዛ ዐይናችሁ ታያላችሁ፤ እናንተም፣ ‘ከእ
ስራኤል ዳርቻ ወዲያ እንኳ እግዚአብሔር
ታላቅ ነው!’ ትላላችሁ::

## እንከን ያለበት መሥዋዕት

6“ልጅ አባቱን፣ ባሪያም ጌታውን ያከብ
ራል፤ እኔ አባት ከሆንሁ፣ መከበሬ የት አለ?
ጌታስ ከሆንሁ መፈራቴ የት አለ? ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት፤ “ካህናት ሆይ፤ ስሜን
የምታቃልሉት እናንተ ናችሁ::
“እናንተ ግን፣ ‘ስምህን ያቃለልነው እን
ዴት ነው?’ ትላላችሁ::
7“በመሠዊያዬ ላይ የረከሰ ምግብ ታስቀም
ጣላችሁ::
“እናንተ ግን፣ ‘ያረከስንህ እንዴት ነው?’
አላችሁ::
“የእግዚአብሔር ገበታ የተናቀ ነው በማ
ለታችሁ ነው:: 8የታወረውን እንስሳ ለመሥ
ዋዕት ስታቀርቡ፣ ያ በደል አይደለምን? አን
ካሳውን ወይም በሽተኛውን እንስሳ መሥዋዕት
አድርጋችሁ ስታቀርቡ፣ ያስ በደል አይደለ
ምን? ያንኑ ለገዢችሁ ብታቀርቡ፣ በእናንተ
ደስ ይለዋልን? ወይስ ይቀበለዋልን?” ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት::
9“አሁን ግን እንዲራራልን እግዚአብሔርን
ለምኑ፤ እንደዚህ ዐይነቱን መሥዋዕት ይዛ
ችሁ ስትቀርቡ ይቀበላችኋልን?” ይላል እግዚ
አብሔር ጸባኦት:: 10“በመሠዊያዬ ላይ ከንቱ
እሳት እንዳታነዱ፣ ምነው ከእናንተ አንዱ
የቤተ መቅደሱን ደጅ በዘጋ ኖሮ! እኔ በእ
ናንተ ደስ አይለኝም፤ ከእጃችሁም ምንም ዐይ
ነት ቍርባን አልቀበልም” ይላል እግዚአብሔር
ጸባኦት:: 11ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግ
ቢያዋ ድረስ፣ ስሜ በሕዝቦች መካከል የከ
በረ ይሆናል፤ በየስፍራውም ሁሉ ለስሜ ዕ
ጣንና ንጹሕ ቍርባን ያቀርባሉ፤ ስሜ በሕ
ዝቦች መካከል የከበረ ይሆናልና” ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት::
12“እናንተ ግን የእግዚአብሔር ገበታ፣ ‘ርኩስ ነው’
ምግቡም፣ ‘የተናቀ ነው’ በማለት ታቃልላላችሁ::
13ደግማችሁም፣ ‘ይህ ድካም ነው’ በማለት በንቀት ጢቅ
አላችሁበት ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት::
“በቅሚያ የመጣውን፣ አንካሳውንና የታ
መመውን እንስሳ ቍርባን አድርጋችሁ ስታቀ
ርቡ ከእጃችሁ መቀበል ይገባኛልን?” ይላል

1፥1 ናሆ1፥1፤
ሐሥ7፥38፤
ሮሜ3፥1-2፤1ጴ4፥11
1፥2 ቊ6:7፤ዘዳ4፥37፤
ኤር46፥27፤ሚል2፥14:
17፤3፥7:13፤ሮሜ9፥13
1፥3 ኢሳ13፥22፤
34፥10፤ሉቃ14፥26
1፥4 ኢሳ9፥10፤
11፥14፤34፥5:11፤
ሰቆ4፥22፤
ሕዝ25፥12-4፤26፥14
1፥5 መዝ35፥27፤
48፥1፤ኢሳ45፥22፤
52፥10፤አሞ1፥11-12፤
ሚክ5፥4
1፥6 ቊ2፤ዘሌ20፥9፤
ዘዳ31፥12፤ኢዮ5፥17፤
ኢሳ1፥2፤ማቴ15፥4፤
23፥9፤ሉቃ6፥46
1፥7 ቊ2:12፤
ዘሌ21፥6፤ሕዝ23፥41
1፥8 ዘፍ32፥20፤
ዘሌ1፥3፤ዘዳ15፥21፤
ኢሳ43፥23
1፥9 ዘሌ23፥33:44፤
መዝ51፥17፤ኤር6፥20፤
ሚክ6፥6–8፤
ሮሜ12፥1፤
ዕብ13፥16
1፥10 ቊ13፤
ዘሌ22፥20፤
2ዜና28፥24፤
ኢሳ1፥11-14፤
ኤር14፥12፤ሆሴ5፥6፤
ሚል2፥12
1፥11 መዝ113፥3፤
ኢሳ6፥3፤12፥4፤
19፥21፤24፥15፤
56፥6፤60፥6-7፤
ማቴ8፥11፤ዕብ13፥15፤
ራእ5፥8፤8፥3
1፥12 ቊ7፤ሕዝ41፥22
1፥13 ቊ10፤
ዘኍ14፥11፤ዘዳ15፥2

1፤ኢሳ43፥22-24
[ሀ]1 ሚልክያስ የስሙ ትርጉም መልእክተኛዬ ማለት ነው::

1፥1 ንግር፤ ዘካ 9፥1 እና ማብ ይመ 12፥1 እንዲሁም ዕን 1፥1 እና ማብ ይመ::

1፥2 ወድጃችኋለሁ፤ እግዚአብሔር ተስፋ ለቈረጠው ለእ ርሱ ሕዝብ የሰጠው ማረጋገጫ ነው::

1፥3 ዔሳውን…ጠላሁት፤ እስራኤል በእግዚአብሔር የቃል ኪ ዳን ፍቅሩ ላይ ጥርጣሬ የሚያድርበት ከሆነ፣ እግዚአብሔር ከእርሷዋ ጋር ያለውን ሁኔታ የያዕቆብ ወንድም ከሆነው ከዔሳው (ከኤዶም) ጋር ካለው ሁኔታ ጋር ማነጻጸር ይኖርበታል:: ጳውሎስ፣ እግዚአብሔር ለያዕቆብ ያለውን ፍቅር፣ በዔሳው ላይ ካለው ጥላቻ ጋር በማነጻጸር ከምርጫ አኳያ አብራርቶታል (ሮሜ 9፥10-13):: እግዚአብሔር ያዕቆብን እንጂ ዔሳውን አልመረጠ ውም:: እዚህ ላይ “መውደድ” እና “ጥላቻ” የሚሉት ቃላት እን ዴት ጥቅም ላይ እንደዋሉ ያዕቆብ ራሔልን አብልጦ ከመውደ ዱና ልያን ከመጥላቱ ጋር ያነጻጽሩ (ዘፍ 29፥31:33 ከዘዳ 21፥16-17 ጋር ያነጻጽሩ):: አማኞችም በዚህ ሁኔታ ከወላጆ ቻቸው ይልቅ (ሉቃ 14፥26) ክርስቶስን አብልጠው መውደድ ይገ ባቸዋል ማቴ 10፥37:: ባድማ፤ ሚልክያስ እዚህ ላይ ስለ ኤዶም የተናገረው፣ ከእርሱ በፊት የነበሩት ነቢያት የተናገሩትን የሚ ያስተጋባ ነው (ኢሳ 34፥5-15፤ ኤር 49፥7-22፤ሕዝ25፥12-14፤35፥1-15፤ አብድዩ ይመ)::ከ550-400 ዓ.ቅ.ክ ባለው ጊዜ ውስጥ የናባጢያን ዐረቦች ኤዶማውያንን ቀስ በቀስ አስለቅቀዋ ቸዋል::

1፥4፤ኤዶምያስ…ይል ይሆናል፤ ከትዕቢቷ የተነሣ በራሷ ብትመካም ይህ ለደኅንነቷ ዋስትና አልሆናትም፤ የወደፊት ዋስ ትናዋንም አያረጋግጥላትም (ከኤር 49፥16 ጋር ያነጻጽሩ)::

1፥5 ከእስራኤል…ታላቅ፤ ተጠራጣሪዋ እስራኤል የኤዶ ምን የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ በምታይበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር አሕ ዛብን ሁሉ የሚገዛ ታላቅ አምላክ መሆኑን አምና ትቀበላለች::

1፥6-2፥9፤ እግዚአብሔር ካህናትን የገሠጸበት ክፍል ነው::

1፥6 ልጅ አባቱን…ያከብራል፤ ከኢሳ 1፥2-3 ጋር ያነ ጻ ጽሩ:: ካህናት…ስሜን የምታቃልሉት፤ ከ2፥5 ጋር ያነጽጽሩ እን ዲሁም ኢሳ 1፥4 ጋር ያነጻጽሩ::

1፥7 ምግብ፤ መሥዋዕት ማለት ነው (ቊ12፤ ዘሌ21፥8: 21ይመ):: ያረከስንህ፤ የረከሰ መሥዋዕት በማቅረብ እግዚአብሔ ርን ራሱን አርክሰውታል:: የእግዚአብሔር ገበታ፤ መሠዊያ ማለት ነው (ቊ12፤ሕዝ44፥16 ይመ):: ካህናቱ የሚበሉት ከመ ሥዋዕቱ ላይ ወስደው ስለሆነ፣መሠዊያው ምግባቸውን የሚያ ገኙበት ገበታ ነው:: የተናቀ፤ አድርገው የእግዚአብሔርን መ ሠዊያና መሥዋዕቱን የተናቀ ነው ብለው እስከቈጠሩ ድረስ (ቊ12)፣ እግዚአብሔርም እነርሱን በሕዝቡ ዘንድ እንዲናቁ ያደርጋቸዋል (2፥9እናማብ ይመ)::

1፥8 የታወረውን…አንካሳውን፤ አካለ ጐደሉ የሆኑ ወይም እንከን ያለባቸውን እንስሳትን እግዚአብሔር ለመሥዋዕትነት አይቀበላቸውም (ዘዳ 15፥21):: ለገዢችሁ፤ ምናልባት የፋርስን ገዢች ማለቱ ሳይሆን አይቀርም::

1፥10 የቤተ መቅደሱን ደጅ በዘጋ፤ የተናቀ መሥዋዕት ከማቅረብ ጨርሶ መሥዋዕት አለማቅረቡ ይመረጣል (ከኢሳ 1፥11-15 ጋር ያነጻጽሩ)::

1፥11 በሕዝቦች መካከል የከበረ፤ ከቊ 14 ጋር ያነጻጽሩ:: የእግዚአብሔር ፍርድ በኤዶምና በሌሎች አሕዛብ ላይ ሲሆን፣ በአማልክቶቻቸው ላይ የእግዚአብሔር ታላቅነት ይገለጣል፤ በዚ ህም የእርሱን ማንነት እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል (ሶፎ2፥11 ይመ):: ዕጣንና ንጹሕ ቍርባን፤ በኢሳ56፥6-7፤60፥7 መጻተኞች የሚያቀ ርቡትን መሥዋዕት እግዚአብሔር እንደሚቀበለው ከሚናገረው ክፍል ጋር ያነጻጽሩ፤ አንዳንድ ሰዎች “ዕጣን” ማለት “ጸሎት” ማለት ነው ይላሉ (ከራእ 5፥8 ጋር ያነጻጽሩ)፤ “መሥዋዕት” የሚለውን “ውዳሴ” (ከዕብ13፥15ጋር ያነጻጽሩ) ማለት ነው ይላሉ::

1፥12፤ የተናቀ…ታቃልላላችሁ፤ቊ7 ይመ::

1፥13፤ በንቀት ጢቅ አላችሁበት፤ በ1ሳሙ 2፥15-17 ላይ

እግዚአብሔር፤ 14“በመንጋው ውስጥ ተቀባይ
ነት ያለው ተባዕት በግ ኖሮት ይህንኑ ሊሰጥ
ተስሎ ሳለ በማታለል ነውር ያለበትን እንስሳ
በጌታ የሚሠዋ ርጉም ይሁን፤ እኔ ታላቅ ንጉሥ
ነኝ፤ ስሜም በሕዝቦች ዘንድ ሊፈራ የሚገባ
ነውና” ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት።

## ለካህናት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

2 “አሁንም ካህናት ሆይ፤ ይህ ማስጠንቀ
ቂያ ለእናንተ የተሰጠ ነው፤ 2ባትሰሙ፣
ልባችሁንም ስሜን ለማክበር ባታዘጋጁ፣
ርግማን እሰድባችኋለሁ፤ በረከታችሁንም ወደ
መረገም እለውጠዋለሁ፤ ልታከብሩኝ ልባች
ሁን አላዘጋጃችሁምና’ ረግሜዋለሁ ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት።
3“ዘራችሁን[a] እገሥጻለሁ[b]፤ የመሥዋታችሁን
ፋንድያ በፊታችሁ ላይ እበትናለሁ፤ እናን
ተም ከእርሱ ጋር ትወገዳላችሁ፤ 4ከሌዊ ጋር
የገባሁት ኪዳን ይጸና ዘንድ፣ ይህን ማስጠን
ቀቂያ የላክሁት እኔ መሆኔንም ታውቃላ
ችሁ” ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት። 5“ከእ
ርሱ ጋር የገባሁት ኪዳን የሕይወትና የሰላም
ኪዳን ነበር፤ እነርሱንም ሰጠሁት፤ ይህም
ክብርን አመጣ፤ እርሱም አከበረኝ፤ ስሜንም
በመፍራትም ጸና። 6እውነተኛ ትምህርት በአፉ
ነበር፤ ምንም ዐይነት የሐሰት ነገር በአንደበቱ
አልተገኘም፤ ከእኔ ጋር በሰላምና በቅንነት ተራ
መደ፤ ብዙዎችንም ከኀጢአት መለሰ።
7“ካህኑ የሁሉ ገዥ፣ የእግዚአብሔር መልእ
ክተኛ ስለ ሆነ ከንፈሮቹ ዕውቀትን ሊጠ
ብቁ፣ ሰዎችም ከአንደበቱ ትምህርትን ሊፈ
ልጉ ይገባል፤ 8እናንተ ግን ከመንገዱ ወጥታ
ችኋል፤ በትምህርታችሁም ብዙዎች እንዲሰና
ከሉ አድርጋችኋል፤ የሌዊንም ኪዳን አፍርሳች
ኋል”ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት። 9“ስለዚህ
በመንገዴ ስላልሄዳችሁና በትምህርታችሁም
አድልዎ ስላደረጋችሁ፣ በሰዎች ሁሉ ፊት እን
ድትናቁና እንድትዋረዱ አድርጌአችኋለሁ።”

## የይሁዳ አለመታመን

10ሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለን
ምን? የፈጠረንስ አንድ ስምላክ አይደለምን?
ታዲያ እርስ በርሳችን ታማኝነት በማጉ
ደል የአባቶቻችንን ኪዳን ለምን እናረክሳ
ለን? 11ይሁዳ አልታመነም፤ በእስራኤልና
በኢየሩሳሌምም አስጸያፊ ነገር ተፈጽሞአል፤
ይሁዳ የባዕድ አምላክ ሴት ልጅ በማግባት
እግዚአብሔር የሚወደውን መቅደስ አርክሶ
አል። 12ይህን የሚያደርግ ማንኛውም ሰው
ቢሆን፣[c] ለእግዚአብሔር ጸባኦት ቍርባን
ቢያመጣም እንኳ፣ እግዚአብሔር ከያዕቆብ
[c] ድንኳን ያስወግደው።
13ሌላው የምታደርጉት ነገር ደግሞ፣ የእግዚ
አብሔርን መሠዊያ በእንባ ታጥለቀልቃ
ላችሁ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ቍርባናችሁን
ስለማይመለከትና በደስታም ከእጃችሁ

1፥14 ዘፀ12፥5፤ ዘሌ22፥18-21፤ ዘዳ28፥58፤ መዝ72፥8-11፤95፥3፤ ኤር46፥18፤አብ1፥21፤ 1ጢሞ6፥15
2፥1 ቍ7
2፥2 ዘኍ6፥23-27፤ ዘዳ11፥26፤28፥20፤ ኤር13፥17፤ምሳ15፥7-9፤ የሐ5፥23፤1ጢሞ6፥16፤ ራእ5፥12-13
2፥3 ዘፀ29፥14፤ ዘሌ4፥11፤1ነገ14፥10፤ ኢዮ9፥31
2፥4 ዘኍ3፥12
2፥5 ዘኍ25፥12፤ ዘዳ14፥23፤28፥58፤3 3፥9፤መዝ25፥10፤10 3፥18፤119፥161፤ ማቴ26፥28፤ሉቃ22፥ 20፤ዕብ7፥22፤12፥28
2፥6 ዘፍ5፥22፤ ዘዳ33፥10፤መዝ25፥21፤ ሉቃ2፥14፤ዮሐ14፥27፤ ሮሜ11፥14፤ገላ5፥22፤ ያዕ5፥19-20
2፥7 ዘሌ10፥11፤ ዘኍ27፥21፤ 2ዜና17፥7፤36፥15፤ ኤር18፥18፤ ማቴ11፥10፤ማር1፥2
2፥8 ዘፀ 32፥8፤ኤር2፥8፤ 18፥15፤33፥21፤ ሕዝ22፥26፤ሆሴ4፥6
2፥9 ዘፀ18፥16፤ ዘሌ19፥15፤1ሳሙ2፥ 17፡30፤መዝ22፥6፤ 35፥4፤ኤር3፥25፤ 51፥37፤ሉሠ8፥32-33፤ 10፥34፤ሮሜ2፥11
2፥10 ዘፀ4፥22፤ 19፥5፤2ነገ17፥15፤ ኢዮ4፥17፤ ኢሳ43፥1፤ ኤር31፥32፤
ሶፎ3፥3-4፤ማቴ5፥16፤6፥4፡18፤ሉቃ11፥2፤1ቆሮ8፥6
2፥11 ዘፀ34፥16፤ ዘዳ4፥37፤ ነህ13፥23፤ኢሳ1፥13፤ 48፥8፤ኤር3፥7-9
2፥12 ዘኍ24፥5፤ 1ሳሙ2፥30-33፤2ሳሙ20፥1፤ሕዝ24፥21፤፤ ሚል፤1፥10
2፥13 መዝ39፥12፤ 66፥18፤ኢሳ58፥2፤ ኤር11፥11፤14፥12

[a]3 ወይም እህላችሁ እንዲጠወልግ አደርጋለሁ።
[b]3 ወይም እቈርጣለሁ፤ የሰብዓ ሊቃናትን ትርጒም ይመ።
[c]12 ወይም ይህን ለሚያደርግ ሰው በመልካም የሚመሰክር ማንም ቢኖር፣ እግዚአብሔር ከያዕቆብ ድንኳን ይቍረጠው።

ከተገለጸው የዔሊን ልጆች ሁኔታ ጋር ያነጻጽሩ። እንካሳውንና... የታመመውን፤ ቍ 8 እና ማብ ይመ።

1፥14፤ *ተስሎ.. ነውር ያለበትን፤* ስእለትን ለማድረስ መሥዋዕት ሆኖ የሚቀርብ እንስሳ ነውርና ነቀፋ የሌለበት መሆን ይገባዋል (ዘሌ22፥18-23ይመ)። *ታላቅ ንጉሥ፤* ዘካ14፥9 ይመ። ስሜም...የሚፈራ ነውና፤ በቍ 8 ላይ ከተጠቀሰው ገዥ ይበልጥ ለማለት ነው (ቍ11እና ማብ ይመ)።

2፥2 *በረከታችሁንም ወደ መርገም፤* በሕዝቡ ላይ የበረ ከትን ቃል መናገር የካህናት ድርሻ ነው (ዘኍ 6፥23-27 ይመ)፤ ሆኖም ግን መባረካቸው ርግማን ከሆነ፣ የእነርሱ ድርሻ ብቻ የሆ ነው የክህነት አገልግሎት ከንቱና ይሆናል።

2፥3 *በፊታችሁ ላይ እበትናለሁ፤* እንዲዋረዱ ለማድረግ ነው። ናሆ3፥6 ይመ። *ፋንድያ፤* ከጋጣ ከብት የሚወጣ አዛባ ወይም የዚህ ስብስብ ቈሻሻ።

2፥4 *ከሌዊ፤* ካህናት የተመረጡት ከሌዊ ነገድ ነው (ዘኍ3፥12-13፤ነህ13፥29)

2፥5 *የሕይወትና የሰላም ኪዳን፤* ከአሮን የልጅ ልጅ ከፊንሐስ ጋር የተደረገውን ኪዳን ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚያመለክት ነው። (ዘኍ25፥10-13ይመ)። ፊንሐስ ከብዔልፌጎር ጋር የተያያዘ የጣዖት አምልኮና ዝሙት የፈጸሙትን ሁለት ሰዎች በመግደል፣ የእግዚአብሔርን ክብር አስጠብቆአል (ዘኍ 25፥1-3)። *አከበረኝ፤* ፊንሐስ ይህን ያሳየው ለእግዚአብሔር ባለው ቅናት ነው (ዘኍ25፥13 ይመ)።

2፥6-7 *ትምህርትን፤* ካህናት የሙሴን ሕግ የማስተማር ኀላፊነት አለባቸው (ዘሌ 10፥11፤ የሶፎ 3፥4፤ ሐጌ2፥11 ማብ ይመ)።

2፥6 *በሰላምና በቅንነት፤* እነዚህ ቃላት በመዝ37፥37 ላይም ተያይዘው ገብተዋል፤ እዚህ ላይ ግን “ከእኔ ጋር በሰላምና በቅንነት ተራመደ” የሚለው ዐረፍተ ነገር የሚያመለክተው ለኪዳኑ ያለውን ታማኝነት ነው።

2፥7 *መልእክተኛ፤* የሕጉ አስተማሪ በመሆኑና በእርሱም አማካይነት ሕዝቡ *የእግዚአብሔርን ፈቃድ* የሚጠይቅ ስለሆነ (የ3፥1 ሐጌ 1፥13 ማብ ይመ)።

2፥8...*ኪዳን አፍርሳችኋል፤* ታማኝነት በጐደለው ማስተማር፤ እንዲሁም ከአሕዛብ ጋር በጋብቻ በመተሳሰራቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል (ዕዝ 9፥1፤10፥18-22፤ነህ13፥27-29 ይመ)። ከሌዊ ጋር፤ ቍ 4 እና ይመ፤ የ5ን ማብ ይመ።

2፥9 *እንድትናቁና፤* በዕብራይስጡ ይኸው ቃል በ1፥7፤12 የ1፥7 ማብ ይመ) ላይ “የተናቀ” ተብሎ ተተርጕሞአል። *አድልዎ ስላደረጋችሁ፤* ይህ በዘሌ19፥15 ላይ ተከልክሉአል። በዚህ ረገድ ካህናት እግዚአብሔርን መምሰል ይገባቸው ነበር (ዘዳ 10፥17 ይመ)።

2፥10-16፤ ሚልክያስ “ታማኝነትን ማጕደል” በሚል ሐረግ ሕዝቡን ይገሥጻቸዋል። ኀጢአታቸውን በተመለከተም በምሳሌነት የሚጠቅሳቸው፤ ሁለት ነገሮች፣ የአሕዛብን ሴቶች ማግባት አንደኛው ሲሆን ፍች ደግሞ ሌላው ነው።

2፥10 *አንድ አባት፤* ኢሳ 63፥16 ይመ። *የፈጠረንስ፤* የተለየ ሕዝቡ አድርጎ ማለት ነው (ኢሳ 43፥1 እና ማብ ይመ)። *የአባቶቻችንን ኪዳን፤* እግዚአብሔር ከቀደሙት አባቶቻቸው ጋር በሲና ተራራ ላይ የገባውን ቃል ኪዳን ማለት ነው። *ታማኝነትን በማጕደል፤* አንድ ሰው የራሱ ወገን የሆኑትን እስራኤላውያንን እንዲሁም እንደ ካህናት ያሉ አገር መሪዎችን እንኳ ማመን ተስኖት ነበር።

2፥11 *የባዕድ አምላክ ሴት ልጅ፤* የአሕዛብን ሴቶች ማለት ነው፤ ከአሕዛብ ሴቶችጋር የሚደረገው እንዲህ ዐይነቱ፣ ጋብቻ ወደ ክህደት የሚወስድ በመሆኑ በኪዳኑ ሕግ አጥብቆ የተከለከለ ነው (ዘፀ34፥15-16፤ዘዳ7፥3-4፤1ነገ11፥1-6 ይመ) እንዲሁም ከኢሱ23፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ)። ዕዝራና ነህምያም ይህን ችግር በጽኑ ታግለውት ነበር (ዕዝ 9፥1-2፤ነህ 13፥23-29)።

2፥12 *ከያዕቆብ ድንኳን፤* ማኅበረ ሰቡን የሚያመለክት ዘይቤያዊ ገለጻ ነው።

ስለማይቀበል ታለቅሳላችሁ፤ ትጮኻላችሁም።
14እናንተም፣ "ለምን ይህ ሆነ?" ብላችሁ ትጠ
ይቃላችሁ። ይህ የሆነው የትዳር ጓደኛህን፣
አጋርህንና የቃል ኪዳን ሚስትህን፣ አታለ
ሃታልና እግዚአብሔር በአንተና በወጣትነት
ሚስትህ መካከል ላለው ቃል ኪዳን ምስክር
ስለ ሆነ ነው።
15እግዚአብሔር አንድ አላደረጋቸውምን?
በሥጋም በመንፈስም የእርሱ ናቸው። ለምን
አንድ አደረጋቸው? ፈሪሀ እግዚአብሔር ያለ
ውን ዘር ይፈልግ ስለ ነበር ነው። ስለዚህ በመ
ንፈሳችሁ ራሳችሁን ጠብቁ፤ ከወጣትነት ሚስታ
ችሁም ጋር ያላችሁን ታማኝነት አታጓድሉ።
16"ፍችን እጠላለሁ" ይላል የእስራኤል አምላክ
እግዚአብሔር ፤ ልብሱን በግፍ ድርጊት የሚሸ
ፍነውንም ሰው[ለ] እጠላለሁ" ይላል እግዚአ
ብሔር ጸባኦት።
ስለዚህ በመንፈሳችሁ ራሳችሁን ጠብቁ፤
ታማኝነታችሁም አይጓደል።

## የፍርድ ቀን

17እግዚአብሔርን በቃላችሁ አታክታችሁታል።
እናንተም፣ "ያታከትነው እንዴት ነው?"
ትላላችሁ?
"ክፉ የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት
መልካም ነው፤ እርሱም በክፉዎች ደስ ይለ
ዋል" ወይም "የፍትሕ አምላክ ወዴት ነው?"
በማለታችሁ ነው።
3 "እነሆ፤ በፊቴ መንገድ እንዲያዘጋጅ
መልእክተኛዬን እልካለሁ፤ የምትፈል
ጉት ጌታ በድንገት ወደ ቤተ መቅደሱ ይመ
ጣል፤ ደስ የምትሰኙበትም የቃል ኪዳኑ መልእክ
ተኛ ይመጣል" ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት።
2እርሱ የሚመጣበትን ቀን ማን ሊቋቋ
መው ይችላል? በሚገለጥበትስ ጊዜ በፊቱ
መቆም የሚችል ማን ነው? እርሱ እንደ
አንጥረኛ እሳት ወይም እንደ ልብስ አጣቢ
ሳሙና ነውና። 3ብርን እንደሚያነጥርና እን
ደሚያነጻ ሰው ይቀመጣል፤ ሌዋውያንንም
አንጽቶ እንደ ወርቅና እንደ ብር ያጠራ
ቸዋል፤ ከዚያም እግዚአብሔር ቍርባንን በጽ
ድቅ የሚያቀርቡ ሰዎች ይኖሩታል፤ 4በዚያ
ጊዜ የይሁዳና የኢየሩሳሌም ቍርባን እንዳ
ለፉት ቀናትና እንደ ቀድሞው ዘመን እግዚ
አብሔርን ደስ የሚያሰኝ ይሆናል።
5"ስለዚህ እኔ ለፍርድ ወደ እናንተ እመ
ጣለሁ፤ በመተተኞች፣ በአመንዝራዎች፣ በሐ
ሰት በሚምሉ፣ የሠራተኞችን ደመወዝ በሚከለ
ክሉ፣ መበለቶችንና ድኻ አደጉን በሚጨ
ቍኑ፣ መጻተኞችን ፍትሕ በሚነፍጉ፣ እኔንም
በማይፈሩት ላይ እመሰክርባቸው ዘንድ እፈ
ጥናለሁ" ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት።

## እግዚአብሔርን መስረቅ

6"እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም፤ ስለዚህ
እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ፤ አልጠፋች
ሁም። 7ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከትእዛዞቼ
ፈቀቅ ብላችኋል፤ አልጠበቃችኋቸውምም፤ ወደ
እኔ ተመለሱ፤ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ"

2፥14 ዘፍ21፥30፤
ኢሱ24፥22፤
ምሳ5፥18፤ሕዝ16፥8፤
ሚል1፥2፤ዕብ13፥4
2፥15 ዘፍ2፥24፤
ዘጸ4፥15፤14፥2፤
ኢሳ54፥6፤
ማቴ19፥4-6፤
1ቆሮ7፥10፡14፤
ዕብ13፥4
2፥16 ዘፍ6፥11፤
34፥25፤ዘዳ24፥1፤
መዝ51፥10፤ምሳ4፥17፤
ማቴ5፥31-32፤19፥4-9፤
ማር10፥4-5
2፥17 ዘፍ18፥25፤
ኢዮ8፥3፤መዝ5፥4፤
ኢሳ1፥14፤
ሕዝ18፥25፤ሚል1፥2
3፥1 ዘኍ27፥21፤
1ሳሙ9፥20፤
2ዜና36፥15፤ኢሳ40፥3፤
42፥6፤ ሚክ5፥2
ማቴ3፥3፤11፥10፤
ማር1፥2፤ሉቃ7፥27
3፥2 1ሳሙ6፥20፤
ኢዮ9፥30፤ኢሳ1፥31፤
30፥30፤ሕዝ7፥7፤
22፥14፤ዳን7፥13፤
ኢል2፥31፤ዘካ13፥9፤
ማቴ3፥10-12፤
16፥27፤ያዕ5፥8፤2ጴጥ
3፥4፤ራእ1፥7፤6፥17
3፥3 1ዜና23፥28፤
ኢዮ28፥1፤መዝ12፥6፤
132፥9፤ኢሳ1፥25፤
ዳን12፥10፤1ቆሮ3፥13፤
1ጴጥ1፥7፤ራእ3፥18
3፥4 2ዜና7፥3፡
12፤መዝ51፥19፤
ሕዝ20፥40፤ሚል1፥11
3፥5 ዘፀ7፥11፤
20፥14፤22፥21፡
22፤ዘሌ19፥11-
12፡13፤ዘዳ24፥19፤
31፥12፤ኢሳ1፥2፤47፥9፤ ኤር7፥9፤ሕዝ22፥7፤ያዕ2፥11፤5፥4፤
2ጴጥ2፥12-14 3፥6 ዘኍ23፥19፤ ኢዮ34፥15፤ ሆሴ11፥9፤
ዕብ7፥21፤ ያዕ1፥17

[ሀ]15 ወይም "ነገር ግን አባታችን በሕይወት እስከ ኖረበት ዘመን ድረስ ይህን አላደረገም። ምን ይፈልግ ነበረ? ይፈልግ የነበረው ከእግዚአብሔር ዘንድ ልጅ ለማግኘት ነበረ።
[ለ]16 ወይም ሚስቱ እንደ ማለት ነው።

2፥13 *ታለቅሳላችሁ፤ ትጮኻላችሁም፤* እግዚአብሔር መሥዋዕታቸውን ስለማይባርክላቸው፣ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያለቅሳሉ።

2፥14 *የቃል ኪዳን ሚስትህን...ምስክር፤* ጋብቻ ቃል ኪዳን ነው። (ምሳ2፥17 ሕዝ16፥8 ይመ)። ቃል ኪዳንም በምስክሮች ፊት ይጸናል (የዘጸ30፥19፤1ሳሙ20፥23፤ኢሳ8፥1-2 ማብ ይመ)።

2፥15 *አንድ፤* ዘፍ 2፥24 እና ማብ ይመ። *ፈሪሀ እግዚአብሔር ያለውን ዘር፤* ጋብቻ ልጆችን "ይቀድሳል" (1ቆሮ7፥14 እና ማብ ይመ)።

2፥16 *ፍችን እጠላለሁ፤* ኢሳ 50፥1 እና ማብ ይመ። *በግፍ፤* 3፥5 ይመ።

2፥17-4፥16፤ እግዚአብሔር ወደ ሕዝቡ እንደሚመጣ ሚልክያስ የተናገረው ትንቢት የሁለተኛው ክፍል አጋማሽ ነው። ሃይማኖትን በተመለከተ አሉታዊ አመለካከት ስላላቸው እንዲሁም በምግባረ ብልሹነታቸው እግዚአብሔርን አድክመውት ስለ ነበር፣ የእግዚአብሔር ወደ ሕዝቡ የሚመጣው ለፍርድ፣ ለማንጻትና ለመቤዠት ነው።

2፥17 እግዚአብሔርን በቃላችሁ፤ አታክታችሁታል፤ በኢሳ 43፥24 ላይ የእስራኤል ኀጢአት እግዚአብሔርን እንዳደከመው ተጽፎአል። *ክፉ የሚያደርግ ሁሉ...መልካም ነው፤* የአሉታዊ አመለካከታቸው ጥልቀት የቱን ያህል እንደሆነ የሚያመለክት ነው። *የፍትሕ..ወዴት ነው?* ከኢሳ5፥19 ጋር ያነጻጽሩ።

3፥1 *መልእክተኛዬን፤* ይህ ቃል በዕብራይስጡ፣ "ማላኪ" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ይህም ነቢይ ወይም ካህን የሚጠራበት ስም ነው። (ሐጌ1፥13እና ማብ ይመ)። ትንቢቱ በመጥምቁ ዮሐንስ መምጣት ተፈጽሞአል (ማቴ11፥10፤ማር1፥2፤ ሉቃ1፥76 ይመ) *መንገድ እንዲያዘጋጅ፤* ጌታ የሚመጣው፣ ለማጥራትና (ቍ3)፤ ለመፍረድ (ቍ5)፤ ነው፤ ነገር ግን ከምሕረቱ የተነሣ ሕዝቡን ለማዘጋጀት ሲል አስቀድሞ መልእክተኛውን ይልካል (4፥5-6እና ማብ እንዲሁም ኢሳ40፥3እና ማብ ይመ)። *የምትፈልጉት ጌታ...ደስ የምትሰኙበትም...ይመጣል፤* ሐጌ 2፥7 እና ማብ ይመ። *የቃል ኪዳኑ መልእክተኛ፤* መሲሑ እግዚአብሔርን በመወከል፣ ቃል ኪዳኑን ይመሠርታል፣ ያጸናልም (የኢሳ 42፥6 ማብ ይመ)።

3፥2 *የሚመጣበትን ቀን፤* የጌታን ቀን ማለት ነው።(4፥1 ይመ። እንዲሁም የኢሳ2፥11፡17፡20 ማብ ይመ)። ሚልክያስ እግዚአብሔር በዓለም ታሪክ ውስጥ የሚያከናውነውን ሥራ፣ በተለይም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸውን ትንቢት ለመፈጸም ጌታ እንደሚመጣ በይፋ ተናግሮአል፤ ይህም በመሲሑ መምጣት ተፈጽሞአል። *መቆም የሚችል ማነው?* የጌታን መምጣት የሚናፍቁ ሰዎች ንጹሕ ልብና የጠራ እጅ ሊኖራቸው እንደሚገባ ማወቅ ይኖርባቸዋል (ከመዝ24፥3-4፣ኢሳ33፥14-15 ጋር ያነጻጽሩ)። *እንደ አንጥረኛ እሳት፤* ኢሳ1፥25፤ ዘካ13፥8-9 እና ማብ ይመ። እንደ ልብስ አጣቢ ሳሙና፤ ኢሳ 7፥23 እና ማብ ይመ። ነጭ ልብስ ንጽሕናን ያመለክታል ከማር 9፥3፤ ራእይ 3፥5 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥3 *ሌዋውያንንም... አንጽቶ፤* በ1፥6-2፥2 ላይ የተገሠጹት፣ የጌታ "መልእክተኞች" እንዲሁም በመሠዊያው ላይ የሚያገለግሉት፣ ከኀጢአታቸውና ታማኝ ካለመሆናቸው ሊነጹ ይገባቸዋል።

3፥4 *ደስ የሚያሰኝ፤* 1፥8 እና ማብ ይመ። እንዳለፉት ቀናትና፤ ምናልባት የሙሴንና የፊንሐስን ዘመን ማለት ይሆናል (የ2፥5 ማብ ይመ)።

3፥5፤ እግዚአብሔር ሲመጣ፣ ጌታ ሌዋውያንን ያነጻል (ቍ3-4) በሕዝቡም ላይ ይፈርዳል። *በመተተኞች፤* በጥንቱ ቅርብ ምሥራቅ አገሮች የተለመደ ነገር ነው (ዘፀ7፥11፤ዘዳ18፥10 ይመ)።

3፥6 አልለወጥም፤ ያዕ 1፥17 ይመ። በሚልክያስ ዘመን የነበሩት ብዙዎች እንደሚያስቡት ሳይሆን፣እግዚአብሔር ምን ጊዜም ለገባው ኪዳን በታማኝነት ጸንቶ የሚገኝ አምላክ ነው። የጠፋችሁ አይደላችሁም፤ ንጽጽሩ ከኤዶም ጋር (1፥3-5) እንዲሁም በእስራኤላውያን ታሪክ ውስጥ እንደሚታየው በታማኝነት ጸንቶ ካለመገኘት ጋር ነው።

3፥7 *ተመለሱ፤ እኔም...እመለሳለሁ፤* ጌታ የሚመጣው እስ

ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት::
"እናንተ ግን፣ የምንመለሰው እንዴት
ነው ትላላችሁ?"
8"ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን?" እና
ንተ ግን ትሰርቁኛላችሁ::
"እናንተ ግን፣ 'እንዴት እንሰርቅሃለን?'
ትላላችሁ::
"ዐሥራትና መባ ትሰርቁኛላችሁ፤ እናንተም፣
መላው ሕዝባችሁም ስለምትሰርቁኝ የተረገ
ማችሁ ናችሁ:: 10በቤቴ መብል እንዲኖር፣
እኔንም በዚህ እንድትፈትኑኝ ዐሥራቱን ሁሉ
ወደ ጐተራ አስገቡ፤" ይላል *እግዚአብሔር*
ጸባኦት፤ "የሰማይን መስኮት የማልከፍት
ላችሁ፣ የተትረፈረፈ በረከትንም ማስቀ
መጫ እስኪታጣ ድረስ የማላፈስላችሁ ከሆነ
ተመልከቱ:: 11ስለ እናንተ ተባዩን እገ
ሥጸለሁ፤ አዝመራችሁን አይበላም፤ ዕርሻ ላይ
ያለ የወይን ተክላችሁም ፍሬ አልባ አይሆ
ንም" ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት:: 12"ከዚ
ያም በኋላ የተድላ ምድር ስለምትሆኑ ሕዝ
ቦች ሁሉ የተባረከ ሕዝብ ብለው ይጠሯ
ችኋል" ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት::
13"በእኔ ላይ የድፍረት ቃል ተናግራችኋል"
ይላል *እግዚአብሔር*::
"እናንተ ግን፣ 'በአንተ ላይ የተናገርነው
ምንድን ነው?' ትላላችሁ::
14"እንዲህም ብላችኋል፤ '*እግዚአብሔርን*
ማገልገል ከንቱ ነው፤ እርሱ የሚፈልገውን
ሁሉ በማድረግና *በእግዚአብሔር* ጸባኦት
ፊት ሐዘንተኞች ሆነን በመመላለስ ምን
ተጠቀምን? 15አሁን ግን ትዕቢተኞችን ቡሩ
ካን እንላቸዋለን፤ ክፉ አድራጊዎች ይበለ
ጽጋሉ፤ እግዚአብሔርን የሚፈታተኑትም ያመ
ልጣሉ::'"
16በዚያን ጊዜ *እግዚአብሔርን* የሚፈሩ ሰዎች
እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ፤ *እግዚአብሔር* አዳ
መጠ፤ ሰማቸውም፤ *እግዚአብሔርን* ለሚፈሩና
ስሙን ለሚያከብሩ በእርሱ ፊት የመታሰቢያ
መጽሐፍ ተጻፈ::
17"እኔ በምሠራበት ቀን እነርሱ የገዛ ገን
ዘቤ[ሀ] ይሆናሉ" ይላል *እግዚአብሔር* ጸባኦት፤
"አባት የሚያገለግለውን ልጁን እንደሚታ
ደግ ሁሉ እኔም እታደጋቸዋለሁ:: 18በዚያን
ጊዜም እንደ ገና በጻድቁና በኀጢአተኛው
መካከል፣ *እግዚአብሔርን* በሚያገለግለውና
በማያገለግለው መካከል ያለውን ልዩነት
ታያላችሁ::

### *የእግዚአብሔር ቀን*

4 "እነሆ፤ እንደ ምድጃ እሳት የሚነድ
ቀን ይመጣል፤ ትዕቢተኞች ሁሉና ክፉ
አድራጊዎች በሙሉ ገለባ ይሆናሉ፤ ያ የሚ
መጣው ቀንም ያቃጥላቸዋል" ይላል *እግዚ
አብሔር* ጸባኦት:: "ሥርም ሆነ ቅርንጫፍ አያስ
ቀርላቸውም::2ስሜን ለምትፈሩ ለእናንተ
ግን የጽድቅ ፀሐይ በክንፎቿ ፈውስ ይዛ
ትወጣለች፤ እናንተም ከጋጥ እንደ ተለቀቀ
እንቦሳ እየቦረቃችሁ ትወጣላችሁ:: 3እኔ በም
ሠራበት ቀን ክፉዎችን ትረግጣላችሁ፤ ከእግ

3፥7 ዘፀ32፥8፤ ኢሳ44፥22፤ ኤር7፥26፤ ሕዝ18፥32፤ ዘካ1፥3፤ሚል1፥2፤ ሐሥ7፥51፤ያዕ4፥8
3፥8 ዘኍ13፥10-12፤ 18፥21፤ዘሌ27፥30፤ ዘካ5፥3፤ሉቃ18፥12
3፥9 ዘዳ11፥26፤ 28፥15-68፣ዘካ5፥3
3፥10 ዘፀ22፥29፤ ዘሌ25፥21፤2ነገ7፥2፤ ነህ13፥12፤ ኢሳ44፥3፤ኢል2፥14፡ 24፤2ቆሮ9፥8-11
3፥11 ዘዳ28፥39፤ ዘፀ10፥15፤ ኢሳ61፥9፤62፥4፤ ሕዝ20፥6
3፥12 ዘዳ28፥3-12፤ 2ዜና31፥10፤ ኢሳ61፥9፤62፥4፤ ሕዝ20፥6
3፥13 ሚል1፥2፤ 2፥17
3፥14 ኢሱ22፥5፤ መዝ73፥13፤100፥2
3፥15 ኢዮ21፥7፤ መዝ14፥1፤119፥21፤ ኤር7፥10
3፥16 ዘፀ32፥32፤ ዘዳ28፥58፤31፥12፤ መዝ33፥18፤34፥15፤ 56፥8፤87፥6፤ ምሳ1፥7፤ሉቃ10፥20፤ ራእ11፥18
3፥17 ዘፀ8፥22፤ ዘዳ7፥6፤ነህ13፥22፤ መዝ103፥13፤ ኢሳ26፥20፤43፥21፤ ሉቃ15፥1-32፤ ሮሜ 8፥14፥21፤ ሉቃ15፥1-32፤ ሮሜ 8፥14፡32፤ ቲቶ2፥14
3፥18 ዘፍ18፥25፤ ዘዳ32፥4፤ማቴ25፥32-33፡41 4፥1 2ነገ10፥11፤ ኢሳ1፥31፤ 2፥2፤5፥24፤31፥9፤ሕዝ17፥8፤ዳን7፥13፤ኢ2፥31፤ ናሆ1፥10፤ማቴ3፥10፤11፥14፤ሐሥ2፥20 4፥2 ዘዳ28፥58፤ ዜና7፥14፤ መዝ61፥5፤111፥9፤118፥27፤ኢሳ9፥2፤ 30፥26፤ 35፡35፥6፤45፥8፤ ማቴ4፥23፤ ሉቃ1፥78፤ ኤፌ5፥14፤ ራእ14፥1፤22፥2
4፥3 ኢዮ40፥12፤ መዝ40-42፤ ሕዝ28፥18

[ሀ]17 ወይም ሁሉን ቻይ፤ "*እኔ በምሠራበት ጊዜ ንብረቴ ይሆናሉ*"

ራኤልን ለመበዝበዝ እስከ ሆነ ድረስ፤ እርሷም ንስሓ መግባት ይገባታል::

3፥9 *የተረገማችሁ፤* 2፥2 እና ማብ ይመ::

3፥10 *ወደ ጐተራ፤* የቤተ መቅደስ ዕቃዎች የሚቀመጡባቸው የተለያዩ ክፍሎች (1ነገ7፥51፤2ዜና31፥11-12፤ ነህ13፥12 ይመ) *የሰማይን መስኮት፤* አባባሉ በሌላ ቦታ የሚያመለክተው የምግብን መትረፍረፍ ነው (2ነገ 7፥2፡19፤ መዝ 78፥23-24 ይመ):: በረከትንም የማላፈስላችሁ፤ ተስፋ የተሰጠበት የቃል ኪዳን በረከት (ዘዳ 28፥12 ይመ)፤ ከኢሳ 44፥3 ጋር ያነጻጽሩ)::

3፥11 *ተባዩን...ፍሬ አልባ፤* የሚያስፈራውን የቃል ኪዳን ርግማን የሚያሳስብ ምሳሌ ነው:: (ዘዳ 28፥39-40)::

3፥12 *የተባረከ ሕዝብ ብለው ይጠሯችኋል፤* ይህ የሚሆነው ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ ሲፈጸም ነው:: (ዘፍ 12፥2-3 ይመ፤) እንዲሁም ኢሳ 61፥9 እና ማብ ይመ)::

3፥14 *እግዚአብሔርን ማገልገል ከንቱ ነው፤* ይህን ያሉበትም ምክንያት እነርሱ የናፈቁት መቤዠት ገና ስላልተፈጸመ ነው:: *ሐዘንተኞች ሆነን፤* ማቅ በመልበስና፤ ዐመድ በመነስነስ ማለት ነው::

3፥15 *ትዕቢተኞችን፤* እግዚአብሔርን የሚፈታተኑ ክፉ አድራጊዎችን ማለት ነው፤ (የመዝ10፥11 ማብ ይመ):: *ቡሩካን፤ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች፣* "የተረገሙ" ብለው የሚጠሯቸውን አይሁድ ግን ባለማመናቸው ምክንያት "ቡሩካን" ብለው ይጠሯቸዋል፤ (መዝ 119፥21 ይመ)፤ አይሁድ ንስሓ ቢገቡ ኖሮ "ቡሩካን" የሚባሉት ሌሎች ሳይሆኑ እነርሱ ራሳቸው ነበሩ (ቍ12):: *ክፉ አድራጊዎች ይበለጽጋሉ...ያመልጣሉ፤* መዝ73፥3፤ 9-12 ላይ መዝሙረኛው የክፉ ሰዎች መበልጸግ እንዴት እንቆቅልሽ እንደሆነበት ይመልከቱ::

3፥16 *እግዚአብሔርን የሚፈሩ፤* ለጥርጣሬና ለአሉታዊ አስተሳሰብ ቦታ ያልሰጡ ማለት ነው:: *እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ፤* በእግዚአብሔር ላይ ማጕረምረም በነገሠበት በዚያ ዘመን ፈሪሀ እግዚአብሔር የነበራቸው ሰዎች ከቍ14-15):: እርስ በርስ መበረታታት እንደሚያስፈልጋቸው ተገንዝበዋል ማለት ነው:: *የመታሰቢያ መጽሐፍ፤* ምድራዊ ነገሥታት መልካም የሆነን ሥራ መዝግበው እንደሚይዙት ማለት ነው:: አስ6፥1-3፤ኢሳ4፥3፤ ዳን7፥10፤ 12፥1 ይመ):: *ስሙን ለሚያከብሩ፤* ከካህናቱ ጋር(1፥2) እና በሕዝቡ መካከል ካሉ አንዳንድ ሰዎች (ቍ14-15፤2፥17) ጋር ያነጻጽሩ::

3፥17 *ገንዘቤ፤* የዘፀ19፥5 ማብ ይመ:: *እታደጋቸዋለሁ፤* በፍርድ ቀን ማለት ነው (4፥1-2 ይመ):: *የሚያገለግለውን፤* ከ1፥6 ጋር ያነጻጽሩ::

3፥18 እንደ ገና...ታያላችሁ፤ ከአሉታዊ አመለካከታቸው የተነሣ አሁን ባያዩትም ማለት ነው 2፥17እና ማብ ይመ::

4፥1 *እንደ ምድጃ እሳት፤* 3፥2-3፤ኢሳ1፥31፤ 66፥15-16 እና ማብ ይመ:: *ቀን፤* የእግዚአብሔር ቀን ማለት ነው(ቍ5፤ 3፥2እና ማብ ይመ):: *ትዕቢተኞች፤* 3፥15 እና ማብ ይመ:: *ገለባ...ያቃጥላቸዋል::* ኢሳ 47፥14 እና የክርስቶስን ሥራ በተመለከተ የመጥምቁ ዮሐንስን ትንቢት ማቴ 3፥12 ላይ ይመ:: *ሥርም ሆነ ቅርንጫፍ፤* ከቃጠሎው የሚተርፍ አንዳች ነገር የለም (ሕዝ 17፥8-9 ይመ)::

4፥2 *የጽድቅ ፀሐይ፤* በኢሳ 60፥1፡19 ላይ እንዲሁም (ማብ ይመ):: እግዚአብሔርና ክብሩ ከፀሓይ ጋራ ተነጻጽረዋል:: ክርስቶስ "ከላይ የመጣ ብርሃን" ነው:: (ሉቃ 1፥78-79፤ እንዲሁም ኢሳ 9፥2 እና ማብ ይመ):: *የጽድቅ...ፈውስ፤* የድነትንና የተሐድሶ ተስፋ እንዳለ ያሳያል ኢሳ 45፥8፤46፥13፤ 53፥5፤ ኤር 30፥17 እና ማብ ይመ):: *በክንፎቿ፤* የፀሓይ ጸዳል (ከመዝ 139፥9ጋር ያነጻጽሩ):: ከታሰረበት ሲፈታ *እንደ ተለቀቀ እምቦሳ፤* የታሰረ እምቦሳ ከታሰረበት ሲፈታና ነጻ ሲሆን ሚዳው አይበቃውም፤ ፈንጭቶም አይደክመውም::

ራችሁ ጫማ በታች ዐመድ ይሆናሉ" ይላል
እግዚአብሔር ጸባኦት።
4"ለእስራኤል ሁሉ ሕጎችና ሥርዐቶች
ይሆኑ ዘንድ፣ ለአገልጋዬ ለሙሴ በኮሬብ የሰ
ጠሁትን ሕግ አስቡ።
5"እነሆ፤ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአ
ብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት፣ ነቢዩ ኤል
ያስን እልክላችኋለሁ። 6መጥቼ ምድርን
በርግማን እንዳላጠፋ፣ እርሱ የአባቶችን
ልብ ወደ ልጆች፣ የልጆችንም ልብ ወደ
አባቶች ይመልሳል።"

4፥4 ዘፀ3፥1፤20፥1፤ ዘዳ28፥61፤መዝ147፥19፤ ማቴ5፥17፤7፥12፤ ሮሜ2፥13፤4፥15፤ ገላ3፥24
4፥5 1ነገ17፥1፤ ኢል2፥31፤ ማቴ11፥14፤ 16፥14
4፥6 ዘዳ11፥26፤ 13፥15፤ ኢሱ6፥17፤23፥15፤ኢሳ11፥4፤ ዘካ5፥3ሉቃ1፥17፤ ራእ19፥15

4፥3 *ክፉዎችን...ትረግጣላችሁ*፤ አንድ ሰው የወይን መጭመቂያን እንደሚረግጥ ማለት ነው (ኢሳ63፥2-3እና ማብ ይመ)።

4፥4 *ሕግ አስቡ*፤ የጌታን መምጣት በትዕግሥት መጠበቅ ላቃታቸው ሰዎች የተሰጠ የመጨረሻ የመንፈስ ማበረታቻ ነው። *ለአገልጋዬ*፤ ዘፀ14፥31፤ ዘዳ34፥5፤ መሳ2፥8፤ መዝ18 ርእስ፤ ኢሳ 20፥3፤41፥8-9፤42፥1 እና ማብ ይመ። *በኮሬብ*፤ የሲና ተራራ ነው (ከዘፀ3፥1 ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥5፤ 3፥1 እና ማብ ይመ። *ኤልያስን*፤ ኤልያስ የፍርድና የመዋጀት አገልግሎት ካገለገለው ከኤልሳዕ በፊት እንደ መጣ ሁሉ፣ ኤልያስም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለጌታ መምጣት ለማዘጋጀት ይላካል። መጥምቁ ዮሐንስም ያገለገለው "በኤልያስ መንፈስና ኀይል" ነው (ሉቃ1፥17፤ማቴ11፥13-14፤17፥12-13፤ማር 9፥11-13 ይመ)። አንዳንድ ሰዎች በራእ 11፥3 ላይ ከተገለጹት ከሁለቱ ምስክሮች አንዱ ኤልያስ ነው ይላሉ። *ታላቁና የሚያስፈራው ... ቀን*፤ ቀኑ 1፤3፥2 እና ማብ፤ ኢዮ 2፥11፡31 ይመ።

4፥6 *ልብ...ይመልሳል*፤ ከዘፍ 18፥19፤ ዘዳ 7፥9-11 ጋር ያነጻጽሩ። በሉቃ 1፥17 መሠረት በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ይህ ተፈጽሞአል። *በርግማን*፤ ፍጹም ጥፋትን የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር ኤዶምን እንደ ቀጣት ሁሉ እስራኤልም ንስሓ የማትገባ ከሆነ፣ እርሷንም ይቀጣታል (ኢሳ 34፥5፤ ከሚል 1፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ)።